# በቋንቋ አገልግሎት ማግኛ ፕሮግራም

ዓላማ

ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ላላቸው/ወይም ምንም ችሎታ ለሌላቸው (LEP/NEP) የዲስትሪክቱ ነዋሪዎች በዲስትሪክቱ የሚሰጡ መረጃዎችንና አገልግሎቶችን በእኩልነት ማግኘታችውን ለማረጋገጥ ነው።

የአሠራራችን ዘዴ

በድንጋጌው መሠረት በቋንቋ አገልግሎት ማግኛ ፕሮግራምን የሚቆጣጠረው የሰብዓዊ መብት ቢሮ (OHR) ነው። የሰብዓዊ መብት ቢሮ ከፍተኛ የሕዝብ ግንኙነት ያላቸው የመንግሥት ፕሮግራሞች፣ መሥሪያ ቤቶች እና አገልግሎት ሰጭዎች ድንጋጌውን በሥራ ላይ እንዲያውሉ የማስተባበርና የቴክኒካል እርዳታ ይሰጣል። በቋንቋ አገልግሎት ማግኛ ቡድኑ ከከንቲባው የላቲኖ ጉዳይ ቢሮ (OLA)፣ የእስያዊና የፓስፊክ ደሴቶች ቢሮ (OAPIA)፣ የአፍሪካኖች ጉዳይ ቢሮ (OAA) እና በቋንቋ አገልግሎት ማግኘት ቅንጅት (DCLAC) - ለስደተኞች ደጋፊ የሆኑ የሕብረተስብ ድርጅቶች ቅንጅት - ጋር በመመካከር ይሠራል።

በሰብዓዊ መብት ቢሮ አመለካከት በዲስትሪክቱ አዘውትረው የሚነጋሩባቸው ቋንቋዎች የሚከተሉት ናቸው፣

የስፓኒሽ    የቻይና    የቬትናም    የኮሪያ    የፈረንሳይ    የአማርኛ

እርዳታ ወይም አቤቱታ ማስገባት ከፈለጉ

በቋንቋ አገልግሎት ማግኛ ፕሮግራም በተጨማሪ በቋንቋ አገልግሎት የማግኘት አቤቱታዎችን የመከታተል፣ የመቆጣጠር እና የመመርመር ኃላፊነት ተሰጥቶታል። አድሎ የተደረገባቸው ወይም መረጃም ሆነ አገልግሎት የተነፈጉ ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው/ወይም ምንም ችሎታ የሌላቸው ነዋሪዎች ወይም ንግድ ያላቸው ግለሰቦች ለሰብዓዊ መብት ቢሮ (OHR) በሚከተለው አድራሻ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ።

## የዲ.ሲ. የስብዓዊ መብቶች ቢሮ

በቋንቋ አገልግሎት ማግኛ ፕሮግራም

Winta Teferi
ፕሮግራም ዳይሬክተር
(202) 727-3942
winta.teferi@dc.gov

ወይም

Gretta Rivero
ፕሮግራም አናሊስት
(202) 727-0892
gretta.rivero@dc.gov

## በቋንቋ አገልግሎት ማግኛ ፕሮግራም ድንጋጌ

የ2004 በቋንቋ አገልግሎት ማግኛ ፕሮግራም ድንጋጌ ዓላማ ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው/ወይም ምንም ችሎታ የሌላቸው (LEP/NEP) የዲስትሪክቱ ነዋሪዎች የሕዝብ አገልግሎቶችን፣ መረጃዎችንና አንቅስቃሴዎችን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከሚያገኙት እኩል እንዲያገኙና እንዲሳተፉ ማድረግ ነው። መረጃዎች ወይንም ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ በዲስትሪክቱ የሚገኙ ኤጀንሲዎች፣ ክፍሎች፣ ወይም ፕሮግራሞች በሙሉ በዚህ ድንጋጌ ይሸፈናሉ። የ2004 በቋንቋ አገልግሎት ማግኛ ድንጋጌና ተመሳሳይ ድንጋጌዎች የዲስትሪክቱ ኤጀንሲዎች ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ላላቸው/ወይም ምንም ችሎታ ለሌላቸው (LEP/NEP) ተገልጋዮች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያስታውቃል። ከታች እንደተጠቀሰው፣ ሁሉም የዲስትሪክቱ ኤጀንሲዎች የሚቀጥሉትን አራት (4) አስፈላጊ ሁኔታዎች ማሟላት እና ከፍተኛ ከሕዝብ ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የተሰየሙ ኤጀንሲዎች ደግሞ ተጨማሪ ሶስት (3) ሁኔታዎችን ማሟላት አለባቸው።

### በድንጋጌው መሠረት ሁሉም የዲስትሪክቱ ኤጀንሲዎች ሟሟላት ያለባቸው

1. በመሠረታዊ የመነጋገሪያ ቋንቋዎች መረጃ መሰብሰብ
2. የአስተርጓሚ አገልግሎቶች መስጠት
3. አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን መተርጎም (በ 3% ወይም 500 ግምት)
4. ከሕዝብ ጋር ግንኙት ያላቸውን ሠራተኞች ተገልጋዮችን እንዴት እንደሚያገልግሉ ሥልጠና መስጠት

### ከፍተኛ የሕዝብ ግንኙንት ያላቸው ኤጀንሲዎች ሟሟላት ያለባቸው

5. የሁለት ዓመት የቋንቋ ማግኛ ፕላን ማዘጋጀት
6. የቋንቋ ማግኛ አስተባባሪ መሰየም
7. የሕዝብ ስብሰባዎች ማዘጋጀት እና ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው/ወይም ምንም ችሎታ የሌላቸውን ሕብረተሰቦች መድረስ (LEP/NEP)

## አግልግሎት ማግኛ አስተባባሪዎች (LAC)

በቋንቋ አገልግሎት ማግኛ ፕሮግራም ከ33 የቋንቋ አገልግሎት ማግኛ አስተባባሪዎች (LAC) ጋር ይሠራል። የቋንቋ አገልግሎት ማግኛ አስተባባሪዎች የማስተርጎም አገልግሎቶች፣ ለኤጀንሲ ሠራተኞች የአፈፃጸም ሥልጠናዎች፣ የሰነዶች መተርጎም እና ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ላላቸው/ወይም ምንም ችሎታ ለሌላቸው (LEP/NEP) እንዲግባቡ በየኤጀንሲዎች በተለያዩ ቋንቋዎች ምልክቶች መኖራቸውን ያረጋግጣሉ።

### ከፍተኛ የሕዝብ ግንኙነት ያላቸው የዲስትሪክቱ ኤጀንሲዎች

የአልኮል መጠጦች ቁጥጥር አስተዳደር
የልጆችና የቤተሰብ አገልግሎቶች ኤጀንሲ
የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የቤቶች ባለሥልጣን
የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሎተሪና በጎ ፈቃድ ጌሞች ቁጥጥር ቦርድ
የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ቤተ መፃህፍት
የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች
የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የተጠቃሚዎችና የቁጥጥር ጉዳዮች መምሪያ
የማረሚያዎች መምሪያ
የአካል ጉዳተኞች አገልግሎቶች መምሪያ
የሠራተኞች አገልግሎቶች መሥሪያ ቤት
የጤና ክፍል
የቤቶችና የማሕበረሰብ ልማት መምሪያ
የሕዝብ ጉዳዮች መሥሪያ ቤት
የሰብዓዊ አገልግሎቶች መሥሪያ ቤት
የአእምሮ ጤና መሥሪያ ቤት
የሞተር ተሸከርካሪዎች መሥሪያ ቤት
የመናፈሻ እና የመዝናኛ መሥሪያ ቤት
የህዝብ ሥራዎች መምሪያ
የጥቃቅንና የሀገር ውስጥ የሥራ ዕድገት መሥሪያ ቤት
የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት
የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የመጓጓዣ መሥሪያ ቤት
የእሳትና የአጣዳፊ ህክምና አገልግሎቶች መሥሪያ ቤት
የአገር ውስጥ ፀጥታና ድንገተኛ አመራር ኤጀንሲ
የአካባቢው የፖሊስ መሥሪያ ቤት
የኮንትራት እና የግዥ ቢሮ
የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ
የዕቅድ ቢሮ
የታክስ እና የገቢ ቢሮ
የሕዝብ መማክርት ቢሮ
የስቴቱ የትምህርት አስተዳዳሪ ቢሮ
የተከራዮች ጥብቅና ቢሮ
የግንኙነቶች ቢሮ
የከልል ቢሮ
የአዛውንቶች ቢሮ